የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

*Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

ግንቦት 27 ቀን 2003 ዓ.ም

# ወያኔ ወንጀለኞችን ለመከሰስ፤ ፍርድ ለመስጠትም ሆነ ምሕረት ለመለገስ መብትም ሥልጣንም የለውም

የጨነቀው እንደተባለው ሁሉ ውድቀቱ አፍጦበት የመጣው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ እዚህ እዚያ እየረገጠና እየደነገገ፣ እየወሰነ እንዳለ ሰሞኑን የሞት ፍርድ የተፈረደባቸውን 23 የደርግ ባለስልጣናት ምህረት አድርጎ የሞት ፍርዱን ሰረዘላቸው የተባለው ማስታወቂያ በቂ ማስረጃ ነው። ከዚህ በፊት የዋጋ ተመን ወሰኛለሁ ብሎ ሲፍጨረጨር ቆይቶ ዛሬ ሰረዝኩት፣ አነሳሁት በማለት የነጋዴውን ክፍል ለመደለል የሚጥረውንም መታዘብ ይቻላል።

ኢሕአፓ ደግሞ ደጋግሞ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ እንዳለው፤ ወያኔ የቀይ ሽብር ወንጀለኞችን ለፍርድ የማቅረብ ሥልጣንም መብትም የለውም። በቅድሚያ ወያኔ እንደ ድርጅት በትግራይ ምድር በቀይ ሽብር ተሳትፎ በርካታ የትግራይ ተወላጆችን የኢሕአፓ አባላት በማለት በመቀሌ፣ አክሱም፣ አድዋ፣ ...ወዘተ አጋልጦ አስገድሏል። በትግራይ ምድር የኢሕአፓ ደጋፊዎችና አባላትን በመጨረስ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት የወያኔ ሰርጎ ገብ ካድሬዎች መሆናቸውም የታወቀ ጉዳይ ነው። ስለዚህም በቀይ ሽብር ወንጀል ወያኔ ራሱ ለፍርድ ይቀርባል እንጂ ሌሎችን ለፍርድ አቅራቢ ሊሆን አይችልም። ዛሬ በወያኔ ትዕዛዝ እየተፃፈ ባለ ተረት-ተረት ትረካ ወያኔ የቀይ ሽብር ሰለባ ነበር ተብሎ ሊለፈፍ ቢሞከርም፤ ወያኔ የቀይ ሽብር ሙዚየም ባለው ውስጥ ያስቀመጣቸው የሬሳ ሳጥኖችም የህወሓት አባላትን አስከሬን የያዙ ነበሩ ተብሎ ቢቀርብም ማንም ሊደብቀው የማይችለው ሐቅ የቀይ ሽብር ዋነኛ ሰለባ ኢሕአፓ እንደነበር ነው። የኢሕአፓ አሳዳጅና ገዳይ ሆኖ ዕድሜ ልኩን ያሳለፈው ወያኔ፤ ለኢሕአፓ አስቦና ተቆርቁሮ ፍትህን ፈለገ ቢባል መቸም ከወያኔ ጀሌዎች ውጪ ማንም ይህን ምፀት ሊያስተናግድ ዝግጁ የሆነ የለም። ወያኔ ወንጀለኛ ብሎ ሌሎችን ሊከስም ሊቀጣም መብትም ሥልጣንም የለውም ያልነው ለዚሁ ነው።

ሕዝብን የፈጀ ወንጀልን በተመለከተ ሊምርም፣ ሊቀጣም የሚችል ሰፊው ሕዝብ፤ በደሉ የተፈፀመበት ሕዝብ ብቻ ነው። በወያኔው ካድሬ ጳጳሰ ነኝ ባይ በሚሰጥ አጓጉል ሽፋን ወንጀለኞችንም ምሕረት ወያኔ ሊሰጥ አይችልም። መላ ኢትዮጵያን በደም ከበከሉት አንዱ የሆነው ተስፋዬ ወልደ ሥላሴና የጎንደርን ሕዝብ ደም ያስለቀሰው አረመኔ መላኩ፤ አጥፈተን ነበር ሲሉ የሰማ ሕዝብ የለም። ዕርቅና ምሕረት ከተባለም ህገወጥ አገዛዝ ባሰኘው ጊዜ ለፖለቲካ ጥቅሙ የሚወስድው እርምጃ ሳይሆን ሕዝብ--በደሉ የደረሰበት ሕዝብ--በቀጥታ የሚሳተፍበት ሂደት መሆን እንዳለበትም ግልፅ ነው። ወንጀለኛ እርስ በርሱ ቢማማር ፋይዳ ቢስ ነው። ከ250 ሺ ያላነሰ ዜጋ በአሰቃቂ መንገድ ተጨፍጭፏል። የፍትሕ ያለ ብሎ የሚጮህ የንፁሐን ደም ዛሬም ፍትህን እየጠበቀ ነው። በህገ ወጥና ወንጀለኛ አገዛዝ እርምጃ ይህ ጩኸት ሊታፈን የሚችልም አይደለም። የተበደለው ሕዝብ ምሕረት ይስጥ፤ ቅጣትን ይፈልግ ገና

ድምፁን የሚያሰማበት ዕድል አላገኘም። ወያኔ የሕዝብን ድምፅና መብት ነጥቆ ባሰኘው ሊደነግግ ቢነሳ ይህ ውሳኔው ዋጋ ቢስ መሆኑን ማወቅ ይገባዋል። የሃይማኖት መሪዎች የተባሉትስ ፍትህን ከፈለጉ ምነዋ የታሰሩት የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ፣ ደብዛቸው የጠፋ እነ ፀጋዬ ገብረ መድህን የት ደረሱ ፣ የሕዝብ መብት ይከበር ሲሉ እስካዘሬ ያልተደመጡ? ይባስ ብለው የመለስን ወንጀል እያጀቡ ያሉ አይደሉምን?

ኢሕአፓ የሰማዕቱን ደም በሕግ መሠረት፣ በሕዝብ ፊት ማስከበሩ የማይቀር ነው – ከሳሽም፣ ቀጪም፣ መሐሪም ሕዝብ ብቻ ነውና።

ፀረ-ሕዝብ የወያኔ መሪዎች ለፍርድ ይቅረቡ!
የቀይ ሽብር ወንጀለኞችን ሕዝብ ይፋረዳቸዋል!!



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France